9ኛ ዓመት ቁጥር 3
9th Year No. 3

ባህር ዳር ታህሳስ 7 ቀን 1996 ዓ/ም
Bahir Dar, 17th December, 2003

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት
ዝክረ ህግ
ZIKRE HIG
Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 5:50
Unit price ------------

ማውጫ

Contents

አዋጅ ቁጥር 92/1996 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአሣ ሃብት ልማት፣ ጥበቃና፣ አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ

Proclamation No. 92/2003
The Amhara National Regional State Fisheries Development, Prevention and utilization Proclamation.

አዋጅ ቁጥር 92/1996 ዓ.ም
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የዓሣ ሀብት ልማት፣ጥበቃና አጠቃቀሙን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

ክልሉ ለምግብነትና ለኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የሚውል የዓሣ ሀብት ክምችት ያለው በመሆኑ ይህንኑ ሀብት በዘላቂነትና ህብረተሰቡን ባሣተፈ መልኩ ለማልማት፣ለመጠበቅና ለመጠቀም የሚያስችል አመች የመቆጣጠሪያ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የዓሣ ሀብት ክምችት በሚገኝባቸው የውሃ አካላት በሙሉ ሀብቱ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት በአግባቡ እንዲለማ፣እንዲጠበቅና ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፍ ለማስቻል ቀደም ሲል ወጥቶ የሚሰራበት የዓሣ ሀብት አጠቃቀም ህግ ባለመኖሩ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3(1)እና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የዓሣ ሀብት ልማትና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 315/1995 ዓ.ም. አንቀፅ 20 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል::

Proclamation No. 92/2003
A Proclamation to provide for the Determination of Fisheries Development, prevention and its utilization in the Amhara National Regional State.

WHEREAS, as the Region has fisheries potential which is utilized for consumption and economic benefits, it is necessary to devise a suitable controlling system to develop, prevent and utilize this resource suitably and with the participation of the public;

WHEREAS, since law of utilizing fisheries resource does not exist so far in order to properly develop prevent and transform the resource to the coming generation being given appropriate attention in water bodies where fisheries potential is available;

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region, in accordance with the power vested in it under the provisions of Article 49 sub-Article 3(1) of the Revised Constitution of the National Region and with the Federal Democratic Republic of Ethiopia Fisheries Development and Utilization Proclamation No. 315/2003 Article 20 sub-Article 2, hereby issues this proclamation.

3. ዓላማዎች

አዋጁ የሚከተሉት አበይት አላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የዓሣ ብዝሀ ህይወትና አካባቢው እንዲጠበቅ፣ የዓሣ ሀብቱ አግባብ በሆኑ የማስገሪያ መሣሪያዎች እንዲመረትም ሆነ ከሚገባው በላይ እንዳይመረት መከላከልና መቆጣጠር፣
2. ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ በሆኑ የውሀ አካላት የአሣ ግብርና ልማትን በማስፋፋት የአሣ ሀብት ለፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ተገቢው አስተዋጽኦ እንዲኖረው ማድረግ፣
3. ጥራቱና ንፅህናው የተጠበቀ የዓሣ ምርት አቅርቦትን ማሣደግና ለምግብ ዋስትና የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ በዘላቂነት ማረጋገጥ፤
4. የዓሣ ሃብቱ የሚገኝበት አካባቢ ሕብረተሰብ ከልማቱ ተጠቃሚ የሚሆንበትንና የሥራ ዕድል የሚያገኝበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር፡፡

4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በክልሉ የግዛት ወሰን ዓሣ በሚረባባቸውና በሚመረትባቸው የውሀ አካላትና የአሣ ምርት ዝግጅትና ግብይት በሚካሄድባቸው ቦታዎች ሁሉ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

ክፍል ሁለት

የዓሣ ሀብት ልማት፣አጠባበቅና አጠቃቀም

5. ከተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሃ አካላት ስለሚገኝ የዓሣ ሀብትና አስግሮቱ

1. ሕጋዊ የዓሣ ማስገር ፈቃድ ያልያዘ ማንኛውም ሰው ከማናቸውም የውሃ አካል ለንግድ ሥራ ዓሣ ማስገር አይችልም፡፡
2. ማንኛውም ሰው ከቢሮው ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር ከጥብቅ የዓሣ ሀብት ልማት ክልሎች ለፍጆታ፣ ለንግድ ወይም ለመዝናኛ ዓሣ ማስገር አይችልም፡፡

3. Objectives

The proclamation shall have the following main objectives:

1. Conserve fish biodiversity and its environment, cultivate fisheries resource with appropriate fishing equipment as well as prevent and control over exploitation of the fisheries resource;
2. Cause fisheries development to have proper contribution to speed, economic growth through the expansion of aquaculture development in natural and man-made water bodies;
3. Increase the supply of safe and good quality fish and ensure a sustainable contribution of the fisheries forwards food security;
4. Create conducive condition that the community found in areas of fisheries resource is to become beneficial and gets job opportunities.

4. Scope of Application

This proclamation shall be applicable to water bodies where fish are bred and cultivated and to all areas where fishing, preparing and marketing takes place within the boundary of the Region.

PART TWO

Fisheries Resource Development, Conservation and Utilization

5. Capture Fisheries from Natural and Man-Made Water Bodies

1. Any person who does not hold a legal fishing permit shall not undertake commercial fishing from any water bodies.
2. Any person shall not under take subsistence fishing, commercial fishing or recreational fishing with in protected fishery resource areas without acquisition of a permit from the Bureau.

3. ማንኛውም ሰው ከቢሮው ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር ከማንኛውም የውሃ አካል ለእርባታም ሆነ ለሌላ ተግባር የአሣ ጫጩቶችን ማስገር አይችልም።

4. ማንኛውም የውጭ ሀገር ዜጋ ለመዝናኛ ዓሣ ለማስገር የሚችለው ከቢሮው ፈቃድ ሲያገኝ ብቻ ይሆናል።

5. ማንኛውም ሰው በልዩ ውል የመጠቀም መብት ከተሰጠው ሰው በቅድሚያ ፈቃድ ሳያገኝ ለፍጆታ፣ ለንግድ፣ ለመዝናኛ ወይም ለምርምር በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 በተጠቀሰው መሠረት ይኸው ውል ከሚመለከተው የውሀ አካል ዓሣ ማስገር አይችልም።

6. ማንኛውም ሰው ሕጋዊ ከሆኑ የማስገሪያ መሣሪያዎች በስተቀር በፈንጂ፣ በጦር መሣሪያ፣ በመርዝና በአደንዛዥ እፅዋት ወይም በኤሌክትሪክ ሞገድ በመጠቀም ከማንኛውም የውሀ አካል ዓሣ ማስገር አይችልም። ዝርዝሩ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

7. ማንኛውም ሰው በክልሉ የግብርና ምርምር ተቋም እውቅና ካላገኘ በስተቀር ከክልሉ የውሀ አካላት ለምርምር ዓሣ ማስገር አይችልም። ሆኖም የምርምር ፕሮጀክቱ ለክልሉ ጠቃሚ መሆኑ ታምኖበት ዕውቅና ከተሰጠው ቢሮው የማስገር ፍቃዱን ሊሰጠው ይችላል።

8. ማንኛውም ሰው ከቢሮው የጽሑፍ ፈቃድ ሳይሰጠው በክልሉ ውስጥ ከሚገኝ አንድ የውሃ አካል ወደ ሌላው የውሃ አካል የዓሣ ዝርያ እንዳያዘዋውር ወይም ከሌላ አካባቢ ወደ ክልሉ እንዳያስገባ ተከልክሏል።

9. ማንኛውም ሰው በክልሉ በሚገኙና መልማት በሚችሉ የውሃ አካላት የአሣ ግብርና ልማት ለማካሄድ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ በማውጣት አልምቶ ተጠቃሚ እንዲሆን ይበረታታል።

10. በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ለመጠየቅ የሚቀርብ ማመልከቻ ለውሳኔ አሰጣጥ እንዲያመች ተፈላጊ ማስረጃዎችን ያሟላ መሆን አለበት። ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ ይገለፃል።

3. Any person shall not undertake the fishing of fingerlings for breeding or any other purpose with out acquisition of a permit from the Bureau,

4. Any foreign national can undertake recreational fishing only upon acquisition of a permit from the Bureau.

5. Any person, without the acquisition of a prior permit from a person granted a right to utilization under special agreement, shall not undertake fishing for subsistence, commerce and recreation or research from water body with which this agreement concerned pursuant to Article 6 mentioned in this proclamation.

6. Any person shall not undertake fishing from water bodies using explosives, ammunitions, poisons and narcotizing plant or electric current except fishing using legal materials. Particulars shall be determined by a directive to be issued by the Bureau.

7. Any person shall not undertake fishing for research from the Regional water bodies without getting recognition from the Regional Agricultural Research Center. However, the Bureau may give him a fishing permit when the research project is believed to be important for the Region and provide with recognition thereof.

8. Any person shall be forbidden to transfer fish species from one water body to another water body in the Region or to import same from another place into the Region without being given a written permit from the Bureau.

9. Any person shall be encouraged to be advantageous through undertaking aquaculture development on exploitable water bodies in the Region by getting a license from a concerned body.

10. An application submitted, in accordance with this proclamation, to request for a license shall fulfill necessary evidences in order to be suitable for decision making. Particulars shall be stated by a directive to be issued for the implementation of this proclamation.

6. የዓሣ ግብርና

1. ከቢሮው የሙያ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር ማንኛውም ሰው ለንግድ ሥራ የዓሣ ግብርና ተቋም መገንባት ወይም የዓሣ ግብርና ማካሄድ አይችልም::

2. ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ ለንግድ ሥራ የዓሣ ግብርና ተቋም መገንባት ወይም ማካሄድ ለሚሻ ማንኛውም ሰው ፈቃድ የሚሰጠው:-

   ሀ. በቂ መሬት ያለውና ለሥራው የሚያስፈልገውን የውሀ መጠን ለመጠቀም ወይም ከመሬት ውስጥ ለማውጣት ወይም በተፈጥሮ የውሀ አካላት ላይ ለመጠቀም አግባብ ካላቸው የመንግስት አካላት የድጋፍ ወይም የትምምን መግለጫ ከክልሉ ፈቃድ የተሰጠው መሆኑ፤

   ለ. የሚቋቋመው የዓሣ ግብርና ተቋም አካባቢን የማይበክል ወይም በተፋሰሱ ባሉ የውሀ አካላት በሚገኙ የዓሣ ዝርያዎች ላይ ጉዳት የማያስከትል መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው::

3. የዓሣ ግብርናና የግብርና ተቋሙን ግንባታና አጠቃቀም ደረጃዎችን በተመለከተ ቢሮው እንደአስፈላጊነቱ መመሪያ ያወጣል::

4. ለንግድ ስራ የአሣ ግብርና ፈቃድ ከቢሮው የወሰደ ማንኛውም ሰው በምርምር የተደገፉ የአሣ ዝርያዎችን በማራባት ጫጩቶችን ለሌሎች ተጠቃሚዎች የማሰራጨት ሀላፊነት አለበት:: ለዚህም ቢሮው ተገቢውን የሙያ ምክር አገልግሎት ይሰጣል::

5. የዓሣ በሽታ ከዓሣ ግብርና ተቋሙ ወደ አካባቢው ሊዛመት ይችላል ተብሎ ሲታመን ቢሮው አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል::

7. የዓሣ ሀብትን ከልዩ ውል በሚመነጭ መብት ስለመጠቀም

ቢሮው በአንድ የውሃ አካል የሚገኝ የዓሣ ሀብት ለአንድ ወይም ለብዙ ሰዎች በልዩ ውል የሚሰጥበትንና የዓሣ ሀብቱ በዘላቂነት መልማቱን የሚቆጣጠርበትን ስርአት በመመሪያ ይወሰናል::

6. Aquaculture

1. Any person shall not build aquaculture facility or undertake aquaculture for commercial purpose without getting work permit from the Bureau.

2. As particulars shall be determined by a directive, a permit shall be issued to any person who seeks to build an aquaculture facility or undertake aquaculture;

   a. Where he has sufficient land and there is acquisition of statement of support or agreement from relevant Regional State bodies to utilize the required amount of water or extract water from the ground or to make utilization on natural water bodies;

   b. When only confirmed that establishment of the aquaculture facility does not pollute the surrounding environment or cause damage on the fish species inhabiting the water bodies in the basing.

3. The Bureau shall, as may be necessary, issue a directive regarding standards for the establishment and utilization of aquaculture and aquaculture facilities.

4. Any person who takes aquaculture license for commercial fishing shall have responsibility to breed fish species substantiated by research and to distribute same to other user. The Bureau shall render the required professional skill counseling service.

5. The Bureau shall take an appropriate measure when it is believed that there is a risk that a fish disease in the aquaculture facility may spread into the surrounding.

7. Utilization of Fisheries Resource From special Agreement with issuance of concession

The Bureau shall determine by directive the issuance of concession of fisheries resource present in water body to one or more than one person as well as the regulation system for sustainable development of the

8. አካባቢን ስለመጠበቅ

1. ማናቸውም የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የዓሣ ሀብት በሚገኝባቸው የውሀ አካላት ሲቀረፁ በዓሣ ሀብቱና በአካባቢው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለማሳደራቸው አስቀድሞ መረጋገጥ አለበት፡፡

2. በክልሉ ውስጥ በሚገኙ ማናቸውም ተፋሰሶች አካባቢ የሚቋቋሙ የተለያዩ ፋብሪካዎችና ሌሎች ተመሳሳይ ተቋማት በተፋሰሱ፣ በዓሣውና በውሀው ውስጥ በሚገኙ ህይወት ባላቸው ነገሮች ላይ በቅድሚያ ጉዳት አለማድረሳቸው በሚመለከተው አካል መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

9. የዓሣ ምርት አያያዝ

በዚህ አዋጅ መሠረት የዓሣና የዓሣ ውጤቶች አያያዝ፣ ዝግጅት፣ ክምችት፣ ማጓጓዝና ንግድ ሥራ ተፈላጊውን የጥራትና የንፅህና ደረጃ የጠበቀ መሆን አለበት፡፡ ቢሮው ይህ ደረጃ የሚወሰንበትን ስርአት በመመሪያ ይወስናል፡፡

10. ስለመረጃ አቅርቦት

ቢሮው ከተለያዩ ምንጮች ስለ ዓሣ ሀብት የሚሰበስባቸውን መረጃዎችና የምርምር ውጤቶች በመገምገምና በማዘጋጀት ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡

ክፍል ሦስት

አዋጁን ስለማስፈፀም

11. የዓሣ ሀብት ተቆጣጣሪ ሥልጣንና ተግባር

1. የዚህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተግባራዊነት ለማረጋገጥ የዓሣ ሀብት ተቆጣጣሪ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ፡-

   ሀ. በማናቸውም የውሀ አካል የሚገኝን ዓሣ አስጋሪ አስቁሞ መፈተሽና ጀልባውንም ሆነ የማስገሪያ መሣሪያውን መመርመር፤

8. Environment Protection

1. It shall be firstly ensured that when any development programs and projects are drawn up in water bodies where fisheries resource present, they will not have a negative impact on fisheries resource and the surrounding.

2. The concerned body shall firstly ensure that different factories and other similar institutions established around in any basins found in the region will not bring damage on the basin, the fisheries resource and all living things in the water.

9. Handing of Fish Products

Fish and fish products handing, processing, storage, transportation and trade shall meet the required standard of fish quality and hygiene in accordance with this proclamation. The Bureau shall determine by a directive the determining procedure for this standard.

10. Providing Fisheries Information

The Bureau shall cause to reach the users by evaluating and preparing the information and research findings, which it gathers from different sources on fisheries.

PART THREE

Enforcement of the Proclamation

11. Powers and Responsibilities of a Fishery Inspector

1. With a view to ensuring the implementation of this proclamation and regulations as well as directives to be issued pursuant to this proclamation, a fishery inspector without a court warrant shall:

   a. Stop and search any fisher found on any water body and inspect the fishing boat as well as gears;

909

ለ. ይህንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች ጥሷል ተብሎ የተጠረጠረ ማንኛውም ሰው ስሙንና አድራሻውን፣ መታወቂያውንና ሌሎች ከዚህ ጋር አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች እንዲሰጠው መጠየቅ፣

ሐ. ማናቸውም ዓሣ የተያዘው፣ የተጓጓዘው፣ ለገበያ የቀረበው፣ ወደ ክልሉ እንዲገባ የተደረገው ወይም ከክልሉ እንዲወጣ የተዘጋጀው ይህንን አዋጅ በመጣስ ነው ብሎ በቂና አጥጋቢ በሆነ ምክንያት ሲያምን ዓሣውን መያዝ፣

መ. ማናቸውም የዓሣ ማስገሪያ ጀልባና መሣሪያ ይህንን አዋጅ በሚፃረር ሁኔታ ጥቅም ላይ መዋሉን አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ ሲያረጋግጥ እነዚህን መሣሪያዎች መያዝ፣

ሠ. ማንኛውም ዓሣ መታመሙ ወይም መበከሉ በማስረጃ ሲረጋገጥ ዓሣው እንዲወገድ ማድረግ፣

ረ. ማንኛውም ሰው ስለተጠቀመበት ማስገሪያ መሣሪያ፣ ስለያዘው ዓሣ አይነትና መጠን እንዲሁም ዓሣውን ስላስገረበት አካባቢ መረጃ እንዲሰጠው መጠየቅ፣

ሰ. ማናቸውም የዓሣ ግብርና፣ የዓሣ ማደራጃ፣ ማከማቻ፣ ማጓጓዣና መሸጫ ተቋማትና መሣሪያዎችን መፈተሽና ተፈላጊውን ደረጃ አሟልተው በማይገኙት ላይ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ ሕጎች መሠረት ከሚመለከተው አካል ጋር በቅንጅት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል።

2. ማንኛውም የዓሣ ሀብት ተቆጣጣሪ፡-

ሀ. በሚጠየቅበት ጊዜ የዓሣ ሀብት ተቆጣጣሪ መሆኑን የሚገልጽ ሕጋዊ የሆነ መታወቂያ ማሳየት፣

ለ. በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚያዙ ማንኛውም ተንቀሳቃሽ ንብረቶች የጽሑፍ ደረሰኝ መስጠት አለበት።

12. ስለተያዘ ዓሣ፣ የማስገሪያ መሳሪያና ሌሎች ዕቃዎች

የዓሣ ሀብት ተቆጣጣሪ፡-

ሀ. በዚህ አዋጅ መሠረት የተያዘና ለገበያ መቅረብ የሚችል ማናቸውም ዓሣ እንዳይበላሽ ለመከላከል በሕጋዊ መንገድ እንዲሸጥ፣ አለበለዚያም ወዲያውኑ እንዲወገድ ያደርጋል፣

b. Demand any person suspected of contravening this proclamation and regulations as well as directives issued pursuant to this proclamation to give his name and address, his identification card and any other relevant information.

c. Seize any fish which the inspector has sufficient and reasonable grounds to believe that the fish has been caught transported, is being marked, imported in to the Region or prepared for export out of the region in contravention of this proclamation.

d. Seize any fishing boat and gear, which the inspector has reasonable grounds to prove that the same has been used in contravention of this proclamation.

e. Destroy any fish, which is proved by evidence that it is diseased or contaminated.

f. Demand any fisher to provide information regarding the gears used, the type and quantity of fish caught, as well as the fishing ground from which the fish were caught.

g. Inspect any aquaculture, fish processing, storage, transport and marketing facilities as well as equipment and cause measures to be taken being integrated with the concerned body pursuant too trade Registration and Licensing laws.

2. Any fishery Inspector shall have to:

a. Show, upon request, a legal identification card which claims that he is a fishery inspector;

b. Provide a written receipt for the seizure of any movable properties pursuant to this proclamation.

12. Regarding seized Fish, Fishing Gears and other Goods

The fishery Inspector shall:

a. Make any seized and marketable fish pursuant to this proclamation be sold legally in order to protect the fish from spoilage, or else make the fish be disposed;

ለ. በዚህ አዋጅ መሠረት የተያዘ የማስገሪያ መሣሪያ ወይም የማጓጓዣና ሌሎች ዕቃዎች ውሳኔ እስኪሰጥባቸው ድረስ በጥንቃቄ እንዲቆዩ ማድረግ ይኖርበታል፤

ሐ. የተያዘ ዓሣ፣ የማስገሪያ መሣሪያ ወይም ሌላ ዕቃ አይነትና መጠን፣ የተያዘበትንና ዓሣው የተሸጠበትን ወይም የተወገደበትን ቀን እንዲሁም ከሽያጭ የተገኘውን ገንዘብ መጠን የሚገልጽ ደረሰኝ ለተያዘበት ሰው ይሰጣል፤

መ. በዚህ አዋጅ መሠረት ዓሣ የተያዘበት ሰው ተቃራኒ ውሳኔ ከፍርድ ቤት ካላመጣ ወይም ክስ መመስረቱን እስከ ሶስት ወር ድረስ ካላሳወቀ ከዓሣው ሽያጭ የተገኘውን ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያደርጋል።

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

13. ወንጀሎች

ማንኛውም ሰው፡-

1. ዝርዝሩ በመመሪያ የሚወሰን ሆኖ ዓሣ ለማስገር በማናቸውም የውሀ አካል ላይ ጎጂ የሆኑ የማስገሪያ መሳሪያዎችን፣ አደንዛዥ ወይም መርዛማ ዕጽዋትን፣ ፈንጂዎችን ወይም የኤሌክትሪክ ንዝረት የሚያስከትሉ መሣሪያዎችን ከተጠቀመ፤
2. ዓሣ እንዳይስገርባቸውሙሉ በሙሉ፣ በከፊል ወይም ለተወሰኑ ወቅቶችና ወራት በተከለከሉና በታገዱ የውሀ አካላት ላይ እገዳውን በመጣስ ማስገሩ ከተረጋገጠ፤
3. ያለፈቃድ ወይም ከተሰጠው ፈቃድ ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ህይወት ያለው ዓሣ ወይም የዓሣ ዕንቁላል ከውጭ ሀገር ካስገባ፣ በክልሉ የውሀ አካላት ከጨመረ፣ ከክልሉ ካስወጣ ወይም ከአንዱ የውሀ አካል ወደ ሌላው የውሀ አካል ካዛወረ፤
4. በኬሚካል የደረቀ ወይም የተጠበቀ ዓሣ ያለፈቃድ ከክልሉ ካስወጣ፤
5. ጥብቅ የዓሣ ሀብት ክልሎችን የሚመለከቱ ማናቸውንም ደንቦችና መመሪያዎች በመተላለፍ ዓሣ ካሰገረ፤

b. Ensure that the fishing gears or transport and other equipment seized pursuant to this proclamation, are well taken care of until a decision is made upon them;

c. Give the person, from whom the fish, fishing gears or other type and quantity of goods were seized, a receipt stating the date of seizure, sale or disposal as well as the amount realized from the sale;

d. Unless the person from whom the fish seized pursuant to this proclamation brings an opposing court ruling or notifies that he files a charge until three months, the proceeds of the fish seized shall be confiscated.

PART FOUR

Miscellaneous Provisions

13. Offences

Any person who:

1. Makes use of, as particulars determined by a directive, harmful fishing equipment, narcotic or poisonous plants, ammunitions or devices causing electric shock for fishing in any water body;
2. Is confirmed that he undertakes fishing in breach of the sanction in water bodies where fishing is forbidden and prohibited completely, partially or for certain seasons and months;
3. Imports live fish or fish eggs from abroad, introduces same in to the Regional water bodies, sends same out of the Region or transfers same from one water body to another without a permit or in contravention to the terms of the permit;
4. Sends out of the Region without a permit the fish which is dried up or kept by chemicals;
5. Undertakes fishing in violation of any regulations and directives concerned with protected fishery areas;

6. ፈቃድ ሳይኖረው ወይም በተሰጠው ፈቃድ ላይ የተገለጹትን ሁኔታዎች በመተላለፍ ከተፈጥሮ የውሀ አካላት ዓሣ ካመረተ ወይም ለንግድ የዓሣ ግብርና ተቋም ከገነባ ወይም ካካሄደ፣

7. የተመጋቢውን ጤንነት ሊያውክ የሚችል የተበከለ ወይም የተመረዘ ዓሣና የዓሣ ውጤቶችን ሲያጓጉዝ ከተገኘ፣ ለገበያ ካቀረበ፣ ለህብረተሰቡ ከሸጠ ወይም ከሰጠ፣

8. በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የሚፈለገውን መረጃ ተጠይቆ ሳይሰጥ ከቀረ ወይም ሀሰተኛና አሳሳች መረጃ ከሰጠ፣

9. የዓሣ ሀብት ተቆጣጣሪ ሥራውን እንዳይሰራ ካሰናከለ፣ ካስፈራራ ወይም ጉዳት ካደረሰ፣

10. ይህንን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች ከተላለፈ ወይም አፈፃፀማቸውን ካደናቀፈ ወንጀል እንደሰራ ይቆጠራል::

14. ስለ ቅጣት

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 ሥር ከተዘረዘሩት ወንጀሎች መካከል አንዱን ወይም ሌላኛውን የፈፀመ ማናቸውም ሰው ድርጊቱ በማስረጃ ሲረጋገጥ ከአንድ አመት በማያንስና ከሶስት አመት በማይበልጥ እስራት ወይም እስከ ብር አስር ሺ በሚደርስ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል::

15. ሌሎች ተጨማሪ እርምጃዎች

1. ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ጥፋተኛነቱ ሲረጋገጥ በተከሳሹ ላይ ከሚወሰነው ማናቸውም አይነት ቅጣት በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ:-

   ሀ. ለወንጀል ተግባር የዋሉት ማናቸውም ጀልባና ወይም የዓሣ ማስገሪያ መሣሪያዎች እንዲወረሱ፣

   ለ. የተያዘ ማናቸውም ዓሣና የዓሣ ውጤት ወይም የተሸጠ ከሆነ ገንዘቡ እንዲወረስ፣

6. Cultivates fish from natural water bodies or builds or undertakes commercial aquaculture without having a permit or in breach of the conditions stated in the given license;

7. Is found transporting, supplying for market, selling or providing for the public contaminated or poisoned fish as well as fish products, which can disturb consumer's health;

8. Fails to provide the required information when demanded or gives false and misleading information pursuant to provisions of this proclamation;

9. Makes trouble, threatens or causes damage on a fishery inspector in order not to carry out his task;

10. Beaches this proclamation or regulations and directives to be issued pursuant to this proclamation or troubles the implementation of same, he is presumed to have committed an offence.

14. Penalty

When any person who has committed one or the other offences among those specified under Article 13 of this proclamation, he shall be punished upon confirmation of the act by evidence with imprisonment for not less than a year and not exceeding three years or with a fine up to Birr 10,000(ten thousand Birr) or with both.

15. Other Additional Sanctions

1. Where any person is convicted of an offence in contravention of this proclamation the court shall, in addition to any other penalty imposed on the accused, order:

   a. The forfeiture of any fishing boat and/or gear used in the commission of the offence;

   b. The forfeiture of any seized fish and fish products or money if same is sold;

ሐ. ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ የዓሣ ማስገር ሥራ ለማካሄድ የዋለ ማናቸውም መርዝ፣ ፈንጂ ወይም ሌላ አይነት መሣሪያ እንዲወረስ፣

መ. የዓሣ አስጋሪነት ሥራ ወይም የንግድ ፈቃዱ እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

2. የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ የተያዙት ዕቃዎች እንዲወረሱ ትዕዛዝ ካልተሰጠ በስተቀር ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ የገንዘብ ቅጣቱ ካልተከፈለ የተያዙት ዕቃዎች ተሸጠው ከሽያጩ በሚገኘው ገንዘብ መቀጮው እንዲሸፈን ይደረጋል።

3. የወንጀል ክስ ከተመሠረተ በኋላ ተከሳሹ በነጻ ቢለቀቅ የተያዘበት ዓሣ ወይም የሽያጭ ዋጋ እንዲሁም የተያዘው የማስገሪያ መሣሪያ ወይም ሌላ ዕቃ ለተከሳሹ ይመለስለታል።

16. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ለዚህ አዋጅ ተግባራዊነት አግባብነት ካላቸው አስፈፃሚ አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት።

17. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ማንኛውም ህግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ከሆነ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተገለጹት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

18. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ ሙሉ ተፈፃሚነት የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል።

19. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ቢሮው ይህንን አዋጅና በአዋጁ መሰረት የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

c. The forfeiture of any poison explosive or any other equipment which has been unlawfully used for fishing;

d. The suspension or cancellation of any fishing activity or fish trade permit.

2. Where, following a conviction, any goods seized are not ordered to be forfeited and if any fines remain unpaid with in 30 days of the conviction such goods may be sold and the proceeds shall be used to cover the fines.

3. Where following a prosecution, when an accused person is acquitted, any seized fish or proceeds realized from the sale of same as well as fishing gear or over goods shall be returned to the person.

16. Duty to cooperate

Any person shall have duty of cooperation with relevant executive bodies for the implementation of this proclamation.

17. Inapplicable Laws

Any law, regulation, directive or customary practice inconsistent with this proclamation shall not applicable on matters stated in this proclamation.

18. Power to Issue Regulation

The Council of the Regional Government may issue regulations necessary for the full implementation of this proclamation.

19. Power to Issue Directive

The Bureau may issue directives necessary for the implementation of this proclamation and regulations to be issued pursuant to the proclamation.

20. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህር ዳር
ታህሳስ 7 ቀን 1996 ዓ.ም

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

20. Effective Date

This proclamation shall come into force as of the date of its publication in the ***Zikre Hig Gazetta*** of the Region.

Done at Bahir Dar
This 17th day of December, 2003.

Yosef Retta
President of the Amhara National Region